# የቤተ ክርስቲያን ማሳሰቢያ

**የሽማግሌ ምትክ ምርጫ**

የሽምግልና አገልግሎት ዘመኑን በሚጨርሰው በወንድማችን ሲሳይ መሸሻ ምትክ ሽማግሌ ለመምረጥ ዛሬ ምርጫው ይደረጋል። እንዲሁም የሽማግሌዎች ሰብሳቢ ከሽማግሌች መካከል ይመረጣል። እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን አመታዊ ሪፖርት የሚቀርብ ይሆናል።

**የ2020 ሪትሪት**

- መቼ፡ July 23-25
- የት፡ Green Lake, Wisconsin (same place as last year)
- More information is coming. Please save the dates.

**የአገልግሎት ጥሪ**

በተለያየ መስክ ለማገልግለ የምትፈልጉ ሽማግሌዎችን አነጋግሩ።

**የአርብ ፕሮግራም**

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፡- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
- ⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**

773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)
630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)
773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)
773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)

**<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>**

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10

# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!




"ገመድ ባማረ ስፍራ ወደቀችልኝ፥ ርስቴም ተዋበችልኝ"
(መዝ. 16:6)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**January 19, 2020** | **ጥር 10፤ 2012 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

**ጸሎት ............................** ወንድም ፍቅሩ ካዩ

**አምልኮ..........................** የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን

**ፕሮግራም መሪ .............** ወንድም ሲሳይ መሸሻ

**ቃል ................................** ወንድም ጌቱ ጳውሎስ

**ማጠቃለያ ......................** ፕሮግራም መሪ

## የሳምንቱ ጥቅስ

“መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ፤
በእያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ መጥገብንና
መራብንም መብዛትንና መጉደልን ተምሬአለሁ።
ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።”
(ፊል. 4:12-13)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7319 N Oakley Ave, Chicago, IL 60645 |
| ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሰኞ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ሲሳይ መሸሻ | | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ኮከቤ አስረስ | | |
| ወ/ም ዘሪሁን/ዮሐንስ | | |
| ወ/ም አያሌው/ጸደቀ | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

**እግዚአብሔር እረኛዬ ነው -- በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።**

የእግዚአብሔር እረኝነት ከሚገለጥበት መንገድ አንዱ የእርሱ መጋቦት ነው። እግዚአብሔር እረኛችን ስለሆነ ይመግበናል። በመዝሙር 23 ዳዊት የእግዚአብሔርን መጋቢነት ሲገልጽ እግዚአብሔር በለመለመ መስክ እንደሚያሳድረውና በእረፍትም ውሃ ዘንድ እንደሚመራው በመተማመን ያውጃል። ይህ መተማመን የመጣው የእግዚአብሔርን መልካም እረኝነት ተለማምዶ ከመወቅ ነው።

በጎች ለመኖር ምግብና ውሃ ያስፈልጋቸዋል። ስለዚህም መልካም የሆነ እረኛ የሚያደርገው አንዱ ነገር በጎቹ እንዳይራቡና እንዳይጠሙ ግጦሽ ባለበት የለመለመ መስክ ያሰማራቸዋል። እንዲሁም በልተው ደግሞ የሚረኩበት ውሃ እንዲያገኙ ተረጋግተው ሊጠጡት ወደ ሚችሉት የእረፍት ውሃ ይመራቸዋል። ጌታ ኢየሱስ በአዲስ ኪዳን እርሱ እውነተኛ “የበጎች በር” እንደሆነ ተናግሯል (ዮሐ. 10:7)። ከሰጠን ተስፋዎች መካከልም “በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፥ ይገባልም ይወጣልም መሰማርያም ያገኛል” የሚል ይገኝበታል (ቁ. 9)። እንግዲህ ወደ ጌታ ስንመጣ ቃሉ “በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል” እንደሚል በዋናነት ድነትን እናገኛለን። ደግሞም ቃሉ “ይገባል ይወጣል” ስለሚል በርሱ አስተማማኝ ጥበቃን እናገኛለን። በመጨረሻም ‘‘መሰማርያም ያገኛል’’ እንደሚል በጌታ ለኑሮ የሚያስፈልገንን እናገኛለን። ጌታ ያድናል፣ ይጠብቃል ደግሞም በመልካም ያሰማራል።

ጌታ የሚያሰማራው በለመለመ መስክ እና በእረፍት ውሃ ዘንድ ነው። ይህ የሚያሳየን በጌታ ስንሆን መጋቦቱ እንዳማይጓደልብን ብቻ ሳይሆን በመጋቦቱ ውስጥ ያለውንም እርካታ ጭምር ነው። መሰማሪያን ማግኘት አንድ ነገር ሲሆን “የለመለመ” መሰማሪያን መግኘት ደግሞ ሌላ ነገር ነው። ልምላሜ ያለበት መሰማሪያ እርካታ ያለበት መሰማርያ ነው። ጌታ በሚሰጠን ነገር ውስጥ ፍላጎታችን ብቻ የሚሟላበት ሳይሆን እረፍትና እርካታ ያለበት ነው። ባለን ነገር ደስ ይለናል። የማጣትና የመጉደል ነገር አይሰማንም።

ከዚህ አንጻር ዛሬ ጌታ አሰማርቶን ባለበት ስፍራ እጅግ በምስጋና እንድሆን ያስፈልገናል። እረኛችን ለኛ የሚስፈልገውን ያውቃል። እርሱ የሰጠን ሕይወት፣ እርሱ የሰጠን ስፍራ፣ እርሱ የሰጠን ትዳር፣ እርሱ የሰጠን ስራ፣ እርሱ የሰጠን ቤት፣ እርሱ የሰጠን ልጆች… ወዘተ መልካም ነው። የለመለመ መሰማሪያ ነው። እረኛችን ባሰማራን ስፍራ በምስጋና እና በደስታ እንሁን። አሁን በአለም ውስጥ ያለው ትልቁ ችግር አለመርካት ነው። ሰዎች ብዙ ነገር እያላቸው አይረኩም። በሞላ ቤት ውስጥ ብቸኝነት ያጠቃቸዋል። አንዳድ ጊዜ ደግሞ ብዙ እያላቸው ጨምረው ብዙ ማከማቸት ይፈልጋሉ። የሰው የፍላጎት ቋት አይሞላም -- የገንዘብ ከርሱ አይጠግብም፣ የስልጣን ጥማቱ አይረካም፣ ያዝና መሻቱ አይቆምም። ለእኛ ግን እንዲህ አይደለም። ጳውሎስ “የምኖርበት ኑሮ ይበቃኛል ማለትን ተምሬአለሁ” (ፊል. 4:11) ብሎ እንዳለ ለኛ አሁን የተሰማራንበት ስፍራ መልካም ነው፤ በቂ ነው፤ የለመለመ ነው። አዳንድ ጊዜ ደግሞ የሰው ፈተና የኋልዮሽ መመልከት ነው። እንዲህ አድርጌ ቢሆን ኖሮ እንዲህ እሆን ነበር እያለ ያለፈው በመሰለው እድል እየተቆጨ ዛሬውን ያበላሻል፤ ነገውንም ያጨፈግጋል። ለኛ ግን እንዲህ አይደለም። ለኛ ዘማሪው “ገመድ ባማረ ስፍራ ወደቀችልኝ፥ ርስቴም ተዋበችልኝ” (መዝ. 16:6) እንዳለ አምላካችን የሰጠን አሁን ያለንበት ኑሮ የተዋበ ነው። እርሱ ለኛ የሚያስባትን ሃስብ ያውቃል -- ፍጻሜና ተስፋ ያለበት የሰላም ኃሳብ ሰጥቶናል (ኤር. 29:11)። አሜን!